የሰበር ችሎት መ/ቁ. 14554

ቀን ታህሣሥ 20 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ ከማል በድሪ

2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

3. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

4. ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

5. አቶ መስፍን እቁበዮናስ

አመልካች፡- ወ/ሮ ጽጌ አጥናፌ - ቀረበች

መልስ ሰጭ፡- ባላምባራስ ውቤ ሺበሺ - አልቀረበም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያፀናው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት እንዲሻር ጠይቀዋል፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ሲሆን ይዘቱም ሲጠቃለል በዚህ መዝገብ የሌሉበት የሰር 2ኛ ተከሣሽ በሆነው ባለቤቴ በአቶ ተስፋዬ ውቤ የተመዘገበውን እና የጋራ ንብረታችን የሆነውን በወረዳ 20፣ ቀበሌ 44፣ የቤ.ቁ. 399 የሆነውን መኖሪያ ቤት የስር 2ኛ ተከሣሽ ባለቤቴ ከአሁን መ/ሰጭ ጋር በመመሳጠር ለአሁን መ/ሰጭ (የስር 1ኛ ተከሣሽ) ለማስተላለፍ የስምምነት ውል አድርገዋል፤ ስምምነቱ መብቴን የሚነካ በመሆኑ ውሉ እንዲፈርስ የሚል ነው፡፡ የስር 2ኛ ተከሣሽ ለክሱ ተቃውሞ እንደሌለው የገለፀ ሲሆን የአሁን መ/ሰጭ በበኩላቸው ክሱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1810 መሠረት በይርጋ ይታገዳል፤ እኔ በሕይወት ያለሁ በመሆኑ ቤቱ ለስር 2ኛ ተከሣሽ በውርስ ተላልፎአል ሊባል አይችልም፤ የቤቱ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር በስር 2ኛ ተከሣሽ ስም ይገኛል ለተባለው ደብተሩ የተገኘው በሀሰተኛ መንገድ



መሆኑን ደብተሩ በስሜ እንዲዛወር የእርቅ ስምምነት ፈርሚል፤ በመሆኑም ቤቱ የራሴ ስለሆነ ክሱ ውድቅ ይደረግ በማለት ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ ቤቱን የአሁን አመልካች እና የስር 2ኛ ተከሣሽ የጋራ ንብረት ነው፤ የስር 2ኛ ተከሣሽም የጋራ ንብረቱን ያለአሁን አመልካች ፈቃድ የማስተላለፍ አይችሉም በማለት የእርቅ ስምምነቱን ውል ፍ/ቤቱ አፍርሶታል በማለት ወሰነ፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ የአሁን አመልካች ባቀረቡት ክስ የአሁን መ/ሰጭ ከስር 2ኛ ተከሣሽ ጋር ያደረጉት ስምምነት መብቴን ስለሚነካ ስምምነቱ ይፍረስልኝ ያሉት ያለአግባብ ነው በማለት የስር ፍ/ቤት ውሣኔን ሽሮታል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም የከፍተኛው ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ በምክንያቱ ባይስማማም በውጤቱ በመስማማት አጽንቶታል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታ ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠውና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባፀናው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ይዘቱም ሲጠቃለል በስር ፍ/ቤት ያቀረብኩት የእርቅ ስምምነት ይፍረስልኝ የሚል ጥያቄ ሲሆን የእርቅ ስምምነቱም ውል እንጅ ውሣኔ አይደለም፤ ከፍተኛ ፍ/ቤቱ በውሣኔው የጠቀሣቸው ድንጋጌዎች ከጉዳዩ ጋር የሚገናኙ አይደለም፤ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ እንዲሻር የሚል ነው፡፡ መ/ሰጭ በበኩላቸው አመልካች ያቀረቡት ክርክር የፍሬ ነገር በመሆኑ በዚህ ሰበር ችሎት የሚታይ አይደለም፤ በተደረገው የእርቅ ስምምነት አመልካች የሌለችበት መሆኑ ክስ መመሥረት አትችልም በማለት አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግ ጠይቀዋል፡፡

በግራ ቀኙ የቀረበው ክርክር ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም ክርክሩን እና አቤቱታ የቀረበበትን ትእዛዝ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር አገናዝቦ መርምሮታል፡፡

በዚህም መሠረት አመልካች የእርቅ ስምምነቱን መሠረት በማድረግ ክስ ለማቅረብ የሚያስችላት የክስ ምክንያት አለ? ወይስ የለም? እና ፍ/ቤት ስልጣን ባለው አካል የተሰጠን የባለቤትነት ማስረጃ ደብተርን ሐሰተኛ በሆነ መንገድ የተገኘ ነው በሚል የመሠረዝ ስልጣን አለው? ወይስ የለውም? የሚሉትን ነጥቦች በጉዳዩ መመለስ ያለባቸው ሆኖ አግኝቷቸዋል፡፡

የስር ፍ/ቤት አቤቱታ ለቀረበበት ውሣኔ መሠረት የሆነውን ውሣኔ የሰጠው አመልካች ባቀረቡት ክስ መነሻነት ነው፡፡ አመልካች ባቀረቡት ክስ የጠየቁት ዳኝነት በአሁን መ/ሰጭና በስር 2ኛ ተከሣሽ መካከል የተደረገው የእርቅ ስምምነት ውል መብቴን የሚነካ በመሆኑ እንዲሻር የሚል ነው፡፡ ይሄም ለክሣቸው መሠረት ያደረጉት እሣቸው የሌሉበትንና በአሁን መ/ሰጭ እና በስር 2ኛ ተከሣሽ መካከል የተደረገውን የእርቅ ስምምነት ውል መሆኑን በግልጽ ያሣያል፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1676(1)መሠረት ስለ ውሎች በጠቅላላ የተደነገጉት ድንጋጌዎች በዚህ ጉዳይ አግባብነት ያላቸው ናቸው፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1808(2) መሠረት ከተዋዋይ ወገኖች ውጭ የሆነ ማነኛውም ጥቅም አለኝ የሚል ሰው ውሉ እንዲሠረዝ የሚጠይቀው ውሉ የተደረገበት ጉዳይ ወይም ምክንያት ከሕግ ውጭ ከሆነ፤ ወይም ለሕሊና ተቃራኒ ወይም ለውል አፃፃፍ የተደነገገው ፎርም አልተጠበቀም በሚል ምክንያት ብቻ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ የእርቅ ስምምነት ውል ተብሎ የተገለፀው የተደረገበት ምክንያት የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር የወጣበትን ስም ማዛወር ሲሆን ይህም ከሕግ ውጭ ወይም ለህሊና ተቃራኒ ነው የሚባል አይደለም፡፡ የእርቅ ስምምነት ውል ነው የተባለው ለውሉ የተደነገገው ፎርም አልተጠበቀም የሚል ክርክር ደግሞ አመልካች አላቀረቡም፡፡ እነዚህ ባልተሟሉበት ሁኔታ አመልካች የሌሉበት (ያልገቡት) ውል ይሰረዝ የሚል ክስ የሚያቀርቡበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት መጀመሪያውኑ የክስ ምክንያት የሌለ በመሆኑ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁ.33 መሠረት አመልካች ክስ ለማቅረብ የማይችሉ ናቸው በማለት ክሱን መዝጋት ነበረበት፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይሄንን ስህተት ሣያስተካክል ያለፈው በአግባቡ አይደለም፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱም ይሄን ስህተት በተመሣሣይ ሁኔታ ማስተካከል ሲገባው አመልካች ባቀረበችው ክስ እንዲሰረዝ የጠየቀችው የእርቅ ስምምነት ውል ሣይሆን ውሣኔ ነው በሚል ይግባኙን ውድቅ ማድረጉን ከትእዛዙ መረዳት ይቻላል፡፡ በመሠረቱ እንዲሰርዝ የተጠየቀው ጠቅላይ ፍ/ቤቱ እንዳለው ውሣኔ ነው ቢባል እንኳን በቤቱ ላይ መብት አለኝ የሚል ወገን በአፈፃፀም ሆነ በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ቤቱን በሚመለከት ክስ ሲያቀርብ አመልካች ቀርበው ከሚከላከሉበት ሁኔታ በቀር ክስ ሣይቀርብባቸው በራሣቸው ክስ በማቅረብ ውሣኔው ይሰረዝልኝ የሚል ጥያቄ የሚያቀርቡበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ይሄም አመልካች የእርቅ ስምምነት ውል ነው ያሉት አንዱ ጠቅላይ ፍ/ቤት ድምዳሜ ውሣኔ ነው ቢባል እንኳን አመልካች ይሰረዝልኝ የሚል ክስ ሊያቀርቡ እንደማይችሉ የሚያመለክት ነው፡፡



በሌላ በኩል ደግሞ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ከፍ ብሎ በተብራራው ምክንያት የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ መሻር ሲገባው ጉዳዩን መርምሮ የስር 2ኛ ተከሣሽ ያገኘው የባለቤትነት ማሰረጃ ደብተር በሐሰተኛ መንገድ የተገኘ ነው፤ በዚህም ምክንያት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1195(1) የተደነገገው የባለቤትነት ማስረጃ ደብተር የያዘ ሰው የቤቱ ባለሀብት እንደሆነ ይቆጠራል የሚለው የህሊና ግምት በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1196(ለ) መሠረት ፈራሽ ሆኗል፤ በመሆኑም የስር 2ኛ ተከሣሽ የቤቱ ባለንብረት ያልሆነ በመሆኑ የእርቅ ስምምነቱ የአመልካችን መብት አይነካም በማለት ነው የስር ፍ/ቤት ውሣኔን የሻረው፡፡ ይሄም ፍ/ቤቱ የአስተዳደር አካል (ክፍል) የሰጠውን የባለቤትነት ማስረጃ ደብተር መሠረዙን ያሣያል፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1196 መሠረት የአስተዳደር ክፍል የሰጠውን የባለበትነት ማስረጃ ደብተር የመሠረዝ ስልጣን እንዳለውና እንደሌለው መመርመሩ አስፈላጊ ነው፡፡ በመሠረቱ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1196 የሚመለከተው አንድ የአስተዳደር ክፍል (አካል) የሰጠው የባለቤትነት ማስረጃ ደብተር በድንጋጌው በተመለከቱት ሁኔታዎች መሆኑን ባረጋገጠ ጊዜ የሰጠውን የባለቤትነት ማስረጃ ደብተር የሚሰርዝበትን አግባብ ነው፡፡ በመሆኑም የሰጠውን የባለቤትነት ደብተር የመሠረዝ ስልጣን ደብተሩን የሰጠው የአስተዳደር አካል እንጅ የፍ/ቤት አለመሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ ቁ.1198(2) አግባብ